DISTRICT OF COLUMBIA
PUBLIC SCHOOLS

# ለትምህርት ቤት አመራሮች፣ ለተፈጠረ-ክስተት ምላሽ-መስጫ መመሪያዎች/Guidelines

## I. ዓላማ/Purpose

ከጠንካራ አመራርነት እና ዓላማ-ካለው ዕቅድ-አወጣጥም ጋር-ቢሆን፣ እያንዳንዱ ስርዓት (system) ወይም ድርጅት - የሰው ወይም የመዋቅር ውድቀትን-የሚያስከትል፣ ከአንድ ወይም ከዚያ-በላይ በሆኑ ግለሰቦች ላይ ኪሳራን ወይም ጉዳትን ሊያመጡ የሚችሉ ክስተቶች ሊያጋጥማቸው ይችላል። እነዚህ ክስተቶች በሚፈጠሩበት ጊዜ-ላይ፣ ለጉዳቱ ማስተካከያ መንገዶችን ለመለየትና ለማስተካከል እንዲቻል እና ስርዓቱ (system)ን ለማጠናከር እና ወደፊት ሊከሰቱ-የሚችሉትን አደጋዎችን ለመግታት አመራሩ-ከገጠሙት ሁኔታዎች ትምህርት እንዲወስድ-ለማስቻል፤ ክስተቱን ለመመልከት የሚያስችል መዋቅር-ያለው አሰራር መኖሩ አስፈላጊ ነው። እነዚህ መመሪያዎች (guidelines)፣ DCPS እነዚህን ግቦች ለመምታት እንዲረዳው፣ ጠንከር-ያለ የአደጋ ግምገማ (risk assessment) እና የክስተት ምላሽ-መስጫ ሂደትን ለመደገፍ-እንዲያስችሉ ተብለው የተዘጋጁ-ናቸው።

| **የአደጋውን መጠን (Degree of Risk) በትርጓሜ-መግለጽ** |
|---|
| **ዝቅተኛ (Low)** - በስርዓቱ (system) ላይ ተጽዕኖ ያለው፣ ነገር-ግን በተማሪው ጤና፣ ደህንነት፣ ወይም ባለው-የደህንነት ጥበቃ ላይ ወዲያውኑ አደጋ-የማድረስ ስጋት የሌለው (ለምሳሌ፤ በቂ-የከፍያ መጠን በውስጡ-የሌለው የ'Kids Ride Free' ካርዶች፣ የመስኮቱ ውሃ-ማስገባት፣ ወይም የቴክኖሎጂ ችግሮች)። |
| **መካከለኛ (Medium)** - በስርዓቱ (system) ላይ ተጽዕኖ ያለው፣ እና በተማሪው ጤና፣ ደህንነት፣ ወይም ባለው-የደህንነት ጥበቃ ላይ አደጋ-የማድረስ አቅም-ያለው ወይም በበርካታ-ተማሪዎች ወይም የመማሪያክፍሎች ላይ ተጽዕኖ ሊፈጥር የሚችል (ለምሳሌ፤ የቡድን አካላዊ የውዝግብ-ጠብ ጥቃት ወይም ለየብቻው-የሆነ የተቋም ችግር፣ እንደ - ውሃ ማፍሰስ በመሳሰሉት-ላይ)። |
| **ከፍተኛ (High)** - በተማሪው ጤና፣ ደህንነት፣ ወይም ባለው-የደህንነት ጥበቃ ላይ ወዲያውኑ አደጋ የማድረስ ስጋት ያለው፤ ጉልህ-የሆነ ጉዳት ገና-አሁን የተከሰተ መሆኑ፣ **ወይም** በአጠቃላይ ትምህርት ቤቱ ላይ ተጽዕኖ የሚፈጥር (ለምሳሌ፤ ተከስቷል ተብሎ-የተጠረጠረ ወሲባዊ ጥቃት፣ ተከስቷል ተብሎ-የተጠረጠረ በአካል-ላይ የደረሰ ቅጣት፣ ሁሉን-አቀፍ የሆነ ተቋማዊ ጉዳይ - እንደ ሙሉ-የሆነው የመገልገያ-አገልግሎት መቋረጥ/utility outage ወይም በቦታው-ሳይገኝ የጠፋ ተማሪ/missing student)። |

## II. ተገቢ-የሆነ እርምጃን-መውሰድ

**አንድ-ነገርን ካያችሁ፣ ተናገሩ (If you see something, say something)። ጊዜውን-በጠበቀ ሁኔታ - የተከናወነውን-ክስተት ሪፖርት-ማድረግ፣ የሁሉም-ሰው ስራ-ነው። ጉዳት-እንዳለ ወይም የጉዳይ-አደጋ መኖሩን ካወቃችሁ፣ ወዲያውኑ ሪፖርት ማድረግ ወሳኝ-ነገር ነው። በአንድነት-ሆነን ግንዛቤ (awareness)ን ማረገገጥ-አለብን፤ በዚህም-መንገድ - ጉዳትን ለመጠገን፣ ወደፊት-ሊደርስ የሚችለውን ጉዳት ለመከላከል፣ እና የማህበረሰብን ደህንነት ለማስጠበቅ የሚችሉ ክትትል-ማድረጊያ እምጃዎችን ለመደገፍ - ያስችለናል።**

### i. የዘወትር-የተለመደ ሪፖርት-አደራረግ (Routine Reporting)

ዝቅተኛ-አደጋ ላላቸው ፈታኝና-አስቸጋሪ ነገሮች - የድርጅቱን ትክክለኛ-አሰራርን-ከመስራት የሚከለክለውን፣ ነገር-ግን ወዲያው-ሊፈጠር የሚችል ጉዳት-የሚያደርስ አደጋን የማያካትት-ለሆነው፤ አሁንም-ቢሆን በኢሜል አማካኝነት ጉዳዩን -መፍትሄ ለመስጠት፣ አስፈላጊ-የሆነ እውቀት ላለው ግለሰብ - ማሳወቅ አስፈላጊ ነው። ትክክለኛ ግለሰብ የትኛው እንደሆነ የማታውቁ-ከሆነ፣ ከዋናው-ተቆጣጣሪያችሁ (supervisor) ጋር ተማከሩ። ይህ ማስታወቂያ፣ እንደ ስርዓት (system) ምላሽ-ሰጪ እንድንሆን ይረዳናል።

### ii. ከፍተኛ-አደጋ ያለው ክስተትን ምላሽ-መስጫ ሪፖርት-አደራረግ (High-Risk Incident Response Reporting)

**ከፍተኛ አደጋ (high risk)**ን ለሚጠቁሙ ክስተቶች፣ የክስተት ምላሽ-አሰጣጥ ፕሮቶኮል/The incident response protocol (ገጽ 3ን ተመልከቱ) - ወዲያውኑ መፈጸም-አለባቸው።

## ክስተትን ሪፖርት-ማድረግ (Incident Reporting): የትምህርት ቤት አመራር - ክትትል-ማድረጊያ ዝርዝር/Checklist

ከዚህ-በታች ከሚያስፈልጉት ማንኛውም ሪፖርት ማድረጊያ ጋር በተጨማሪ-ሆኖ፣ የመጀመሪያ ሪፖርት-ማድረጊያ እና የአደጋው ግምገማ - ወዲያውኑ መጠናቀቅ አለበት። ከፍተኛ-አደጋ ምላሽ-አሰጣጥ ዕቅድ-አወጣጥ፣ በዚያኑ ችግሩ-በታወቀበት የስራ-ቀን ላይ - ከማዕከላዊ ቢሮ የክስተት ምላሽ-አሰጣጥ ፕሮቶኮል/central office incident response protocol ጋር-ጎን ለጎን ሆኖ መከናወን-አለበት (የሚቀጥለውን-ገጽ ተመልከቱ)። ***የትኛውን እርምጃዎች መውሰድ-እንዳለባችሁ ግልጽ-ካልሆነላችሁ፣ እባካችሁ - ዋናው-ተቆጣጣሪያችሁ (supervisor)ን አማክሩ።***

**<u>ክፍል/Part 1: *ሁሉንም ክስተቶች-በተመለከተ፣ የውስጥ-አሰራር ሪፖርት-ማድረጊያ መስፈርቶች* (Internal Reporting Requirements)</u>**

☐ከበላያችሁ ያለውን ተቆጣጣሪ (immediate supervisor.) ማነጋገር። ከበላያችሁ-የሚገኘው ተቆጣጣሪ (immediate supervisor) የማይኖር-ከሆነ፣ የትምህርት ቤቶች ሹሞቻችሁን ማነጋገር።

☐የክስተት ሪፖርቱ ወደ ስርዓቱ (system) መግባቱን ለማረጋገጥ፣ የትምህርት ቤታችሁን የጥበቃ-ሹም (security officer)ን ማነጋገር።

☐የትምህርት ቤት የቀውስ-ዕቅድን (crisis plan) እንዲጀመር-ማድረግ፣ እንደየአስፈላጊነቱ።

☐ክስተቱ/incident - ማንኛውንም የDCPS ተቀጣሪ-ሠራተኛን የሚያካትት ከሆነ፣ የሰራተኛ አስተዳደር እና የቅጥር-ግንኙነቶችን (Labor Management and Employee Relations (LMER)ኝ በ: dcps.lmer@dc.gov ማነጋገር

**<u>ክፍል/Part 2: *ተጨማሪ የሪፖርት-አደራረግ መስፈርቶች* (*እውነታ-ተኮር*/Fact-Specific):</u>**

A. <u>የሚከተሉትን ለሚያካትቱ ክስተቶች:</u>
  - **ጥቃት/VIOLENCE**
  - **የህክምና የአስቸኳይ-ጊዜ እርዳታ/MEDICAL EMERGENCIES**
  - **ወንጀል/CRIME**

  ☐**ወዲያውኑ 911**ን ማነጋገር።

  ☐የDCPS የፖሊስ ኮማንደር ማዕከልን - ማነጋገር: (**202) 576-6950**

B. <u>የሚከተሉትን የውንጀላ-ክስን ለሚያካትቱ ክስተቶች:</u>
  - **ወሲባዊ ጉዳት (SEXUAL ABUSE)፣ ትንኮሳ/ASSAULT፣ ወይም ጥቃት/VIOLENCE**
  - **ለወሲብ ከቦታ-ወደቦታ ማዘዋወር (SEX TRAFFICKING)/የወሲብ ድርጊትን መግለጽ/ብዝበዛ (SEX ACT DEPICTION/EXPLOITATION)**

  ☐የሜትሮፖሊታን ፖሊስ መምሪያ (Metropolitan Police Department (MPD)ን ማነጋገር

  ☐የDCPS የፖሊስ ኮማንደር ማዕከልን - ማነጋገር: (**202) 576- 6950**

  ☐የልጅ እና ቤተሰብ አገልግሎቶች አስተዳደር (Child and Family Services Administration (CFSA)ን ማነጋገር: **(202) 671-SAFE**

  ☐የ'ማዕከላዊ-ቢሮ የCARE ቡድን'ን ማነጋገር: **(202) 442-5405 ወይም ኢሜል** dcps.care@dc.gov

C. <u>የሚከተሉትን የውንጀላ-ክስን ለሚያካትቱ ክስተቶች:</u>
  - **ማንጓጠጥ(BULLYING)/የሳይበር-ማንጓጠጥ(CYBER BULLYING)፣ ፆታዊ-አድልዎአዊ ጥቃት/GENDER-BASED HARRASSMENT**
  - **ማዋረድ-ማቃለል (HAZING)፣ ጠበኝነትን-ፈጣሪ የሆነ አካባቢ (HOSTILE ENVIRONMENT)፣ እንዲፈሩ-ማድረግ (INTIMIDATION)**
  - **'ኩዊድ-ፕሮ-ኮ/QUID-PRO-QUO' ትንኮሳ/HARRASMENT፣ የበቀል-እርምጃ/RETALIATION፣ ወሲባዊ ትንኮሳ/SEXUAL HARRASMENT**

  ☐የ'ማዕከላዊ-ቢሮ የCARE ቡድን'ን ማነጋገር: **(202) 442-5405**

  ☐የDCPS የፖሊስ ኮማንደር ማዕከል/Police Command Centerን - ማነጋገር: **(202) 576- 6950**

DISTRICT OF COLUMBIA
PUBLIC SCHOOLS

# የDCPS ማዕከላዊ ቢሮ የከፍተኛ-አደጋ ክስተት (Central Office High-Risk Incident) ምላሽ-አሰጣጥ ፕሮቶኮል/Response Protocol

## ደረጃ/Stage 1: ክስተትን ማግኘት/ሪፖርት-ማድረግ (Incident Discovery/Reporting)

**የርዕሰ-መምህር ሚና/Principal Role:**
የትምህርት-አሰጣጥ እርዳታ (Instructional Supt. (IS)ን እንዲያውቁት-በማድረግ ማንቃት/Alert፣ እና ክንውኖች/operationsን እንዲያውቁት-በማድረግ ማንቃት/alert። የትምህርት ቤት የጥበቃ-ሹም (security officer) - የክስተት ሪፖርት/incident reportን ማስገባቱን፣ ማረጋገጥ። የትምህርት ቤት የቀውስ-ምላሽ አሰጣጥ ዕቅድን (school crisis response plan) እንዲጀመር-ማድረግ፣ እንደየ-አስፈላጊነቱ።

**911ን እንዲያውቀው-በማድረግ ማንቃት፣ እንደየ-አስፈላጊነቱ--**
ጥቃት-ፈጣሪ ክስተቶች፣ ጉዳት-የሚያደርሱ አደጋዎች፣ የሕክምና የአስቸኳይ ጊዜ ሁኔታዎች፣ ወንጀል
911 እንዲያውቀው-የሚያደርገው ማንቂያ ከተደረገ፣ ሁልጊዜ ወደ 'DCPS Security' መደወል።

**ለ'CFSA' እና 'MPD' በማንቃት-ማሳወቅ፣** እንደየ-አስፈላጊነቱ--የልጅ ጥቃት (child abuse) ወይም ቸልተኝነት (neglect) ጥርጣሬ-መኖርን ማስታወሻ: ሁለቱም - ተቀጣሪ-ሠራተኛ እና ተቆጣጣሪ (supervisor) - ወደ 'CFSA' (202-671-SAFE) እና 'MPD' - መደወል-ያስፈልጋቸዋል።
ልጁ፣ በትምህርት ቤቱ ቃለ-መጠይቅ በማድረግ መጠየቅ-የለበትም።

**እንደየአስፈላጊነቱ የ'CARE' ቡድንን ማነጋገር--**
ሊከሰት-የሚችል የ'Title IX V' ጥሰት (ተከስቷል-የተባለ ተገቢ-ያልሆነ ወሲባዊ ተግባር)፣ ወደ 202-442-5405 መደወል።

## ደረጃ/Stage 2: ክስተትን ማጋራት እና ዝርዝር-ሁኔታዎችን መሰብሰብ (ወዲያውኑ/Immediate)

**የክንውኖች ሚና/Operations Role:**
1) ለማዕከላዊ ቢሮ (Central Office) አመራር - ሪፖርት-የተደረገው መረጃን፣ ማስታወቂያ/Notification፣ የመጀመሪያ-ደረጃ (Elementary)/ሁለተኛ-ደረጃ (Secondary) ሹም/Chief፣ እና 'IS'
2) በትምህርት ቤት ላይ ያደረሰው ተጽዕኖ - ትንታኔ/Analysis
3) ለትምህርት ቤቱ ወዲያውኑ የተሰጠው የጥበቃ/security እና የክንውኖች እርዳታ/operations support

**የመጀመሪያ-ደረጃ (Elementary)/ሁለተኛ-ደረጃ (Secondary) ትምህርት ቤቶች ሹም፣ ሚና/Role:**
1) ከክንውኖች (operations) ጋር ወዲያውኑ የተደረገ የማማከር-ስራ/consultation
2) ከ'IS' እና ርዕሰ-መምህር ጋር፣ እርዳታ-ለመስጠት የተደረገ ግንኙነት/Communication
3) ከማዕከላዊ ቢሮ (Central Office) አመራር እና ቡድኖች ጋር (እንደየ-አስፈላጊነቱ) የተደረገ - የክትትል-ማድረጊያ የምላሽ-አሰጣጥ ማስተባበሪያ

**የተገኙ-ውጤቶች/Outcomes:**

1) **ወዲያውኑ-የሚደረግ የጥበቃ/safety እና የክንውናዊ እርዳታ/operational support - ለትምህርት ቤት**
2) **የማዕከላዊ ቢሮ አመራሮች እና የቡድን አባላቶች/Central Office leadership and team members እንዲያውቁ-ተደርጓል (ግንዛቤ/awareness)**
3) **ተጨማሪ የማዕከላዊ ቢሮ አስተባባሪ (አስፈላጊነቱ በተጠቆመ-ጊዜ)**

## ደረጃ/Stage 3: እርዳታ/Support እና በዚያኑ-ቀን ላይ የሚደረግ ዕቅድ/Same Day Plan (በ2 ሰዓታት ውስጥ)

**የመጀመሪያ-ደረጃ (Elementary)/ሁለተኛ-ደረጃ (Secondary) ሹም/Chief እና 'IS' ሚና/Role:** የእርምጃ-አወሳሰድ ዕቅድ-አወጣጥን መስራት እና ከርዕሰ-መምህር/principal ጋር በትብብር-መስራት እና በትምህርት ቤት ውስጥ በክንውናዊ-ሂደት ውስጥ መገዛት (procedural compliance)

**የግንኙነት-ማድረጊያዎች ሚና/Communications Role:** ለትምህርት ቤት፣ የባለ-ድርሻ ግንኙነት-ማድረጊያዎች (stakeholder communications)/አዲስና-ማሻሻያ የተደረገላቸው እና የሚዲያ መግለጫዎች (updates and media statements)ን - በዚያኑ-ቀን ላይ የሚደረግ ግንኙነት/same day communicationን መቅረጽ

**የክንውኖች ሚና/Operations Role:** ቀጣይነት-ያለው የክስተት ምላሽ-አሰጣጥ እርዳታ፣ ከሌሎች ኤጀንሲዎች ጋር በቅንብር-መስራት (MPD, DGS, Pepco, ወዘተ...)

**የአጠቃላይ ካውንስል ሚና/General Counsel Role:** ህጋዊ ካውንስል/Legal counsel፣ የፖሊሲ መመሪያ/policy guidance፣ የግንኙነት-ማድረጊያ ምልከታ/communications review (አስፈላጊ-በሚሆን ጊዜ)

**የተማሪ እርዳታዎች ሚና/Student Supports Role:** የአሰቃቂ-ጉዳት ግምገማ/Trauma assessment እና ተጨማሪ የቀውስ-ጊዜ ምላሽ-ሰጪዎች/crisis responders አቅርቦት (በሚያስፈልግ-ጊዜ)

**የሠራተኛ አስተዳደር (Labor Management) እና የተቀጣሪ-ሠራተኛ ግንኙነቶች ሚና (Employee Relations Role):** ምርመራ-ማድረግ (Investigation)፣ ለተተኪ-ሠራተኞች አመዳደብ/substitute staffing ድጋፍ-መስጠት (አስፈላጊ-በሚሆን ጊዜ)

**የቤተሰብ ተሳትፎ ሚና/Family Engagement Role:** እርዳታ እና መመሪያ - እነዚህን-በተመለከተ: የማህበረሰብ ተጽዕኖ/community impact (አስፈላጊ-በሚሆን ጊዜ)

**የተገኙ-ውጤቶች (Outcomes):**
1) **በዚያኑ-ቀን የተደረገ ዕቅድ (Same day plan)፣ ከማዕከላዊ ቢሮ አመራር እና ቡድኖች ጋር - ግንኙነት-ተደርጎ/communicated ተሰጥቷል**
2) **የትምህርት ቤቶች እርዳታዎች ሹም (Chief of Schools supports) - መደበኛ አዲስና-ማሻሻያዎች/regular updatesን - ያቅዳል እና ያቀርባል**

DISTRICT OF COLUMBIA
PUBLIC SCHOOLS

# የተቀጣሪ-ሠራተኞች የስነምግባር ጉድለት ክስ፣ የግንኙነት-ማድረጊያ ሂደት

I. **መግለጫ (Description)—**ይህ ሰነድ፣ ተማሪዎችን የሚያካትቱ የስነምግባር ክሶች፣ በዲሲ የሕዝብ ትምህርት ቤቶች ተቀጣሪ-ሠራተኞች እና/ወይም አጋር (partner) ወይም አገልግሎት-አቅራቢ ሠራተኞች ላይ ሲቀርቡ፤ የትምህርት ቤት ማህበረሰቦች - የመልዕክት ግንኙነት-ማድረጊያ ልውውጥ ሂደቶችን - የሚገልጽ ነው።

II. **ዓላማ (Purpose)—**ከወላጆች፣ ቤተሰቦች እና ማህበረሰቦች ጋር - ከባድ-የሆኑ የሠራተኞች የስነምግባር ክሶች በሚነሱበት-ጊዜ፣ ግልጽነትን ለማራመድ የታቀዱ ሲሆን - የተቀጣሪ ሠራተኛ መረጃን ሚስጢራዊነት እና በንቃት-የሚከናወኑ ምርመራዎችን - በተገቢው-ሁኔታ በማስጠበቅ-ላይ እንዲያገለግሉ የታሰቡትን - የሚያበረታታውን የግንኙነት-ማድረጊያ ሂደቶችን ይተረጉማል።

III. **መልዕክት-አላላክ/Messaging**

- የሚከተሉት የአደጋ ዓይነቶች፣ የተቀጣሪ-ሠራተኛ ጉዳዮችን - ከማህበረሰቡ ጋር በሚመለከት፣ የሕዝብ ግንኙነት-ማድረግ (public communication) ሊያነሳሱ ይችላሉ:
  - የሠራተኛ አባልን - ዕረፍት-እንዲዋጣ ያደረገውን ምክንያት፤ ጉልበትን-የመጠቀም (use of force) ወይም በአካል-ላይ ጉዳት የማድረስ ቅጣት (corporal punishment) ተካሂዷል ተብሎ-ክስ የቀረበበት ሪፖርቶች፤
  - የሠራተኛ አባልን - ዕረፍት-እንዲዋጣ ያደረገውን ምክንያት፤ ተገቢ-ያልሆነ ወሲባዊነት በባህሪው ውስጥ አለ- ተብሎ-ክስ የቀረበበት ሪፖርቶች፤ እና/ወይም
  - ከላይ-ከተጠቀሱት ከአንደኛው-ክሶች ጋር ግንኙነት-ባለው ሁኔታ፣ ይህም የሠራተኛ-አባሉን ዕረፍት-እንዲወጣ ምክንያት ባደረገው-ሁኔታ ሳቢያ - መያዝና-ማሰር/Arrests።

- የሚከተለው መረጃ፣ ተማሪን በአካተተ ሁኔታ አለአግባብ-የሆኑ የተቀጣሪ-ሠራተኛውን ክሶች በተመለከተ - በሕዝብ መልዕክት-መላኪያ (public messaging) ውስጥ ሊካተት-ይችል ይሆናል።
  - የሠራተኛ አባል የስራ-ድርሻ (ከትምህርት-ቤት ውጪ ያሉ እንቅስቃሴዎች/extracurricularsን ጨምሮ)፤
  - የክሱ ባህሪይ/Nature of the allegation፤
  - የሠራተኛ አባሉ ዕረፍት-እንዲወጣ የተደረገ-መሆኑን ማረጋገጫ/Confirmation፤
  - ጉዳዩ ወደ የልጅ እና ቤተሰብ አገልግሎቶች ኤጀንሲ (Child and Family Services Agency (CFSA) ሪፖርት-የተደረገ መሆኑን ማረጋገጫ/Confirmation፤ እና/ወይም
  - ጉዳዩ ወደ ሜትሮፖሊታን ፖሊስ መምሪያ (Metropolitan Police Department (MPD) ወይም ወደ-ተገቢ የሆነ የህግ-አስከባሪ ኤጀንሲ የተመራ-መሆኑን ማረጋገጫ/Confirmation፣ የተፈቀደ-ከሆነ/if permitted።
  - ለእስር-በተያዘበት ጊዜ - የሠራተኛ-አባሉ ስም፣ ይህ ካለ (if applicable)።

IV. **የሂደቱ አጠቃላይ-ምልከታ (Process Overview)—**የሠራተኞች የስነምግባር ጉድለት ክስ በሚገለጽበት ጊዜ፣ የግንኙነቶች ቡድን (Communications Team) ከብዙ ቡድኖች እና ኤጀንሲዎች ጋር በመሆን፣ በሚቀጥለው የትምህርት-ቀን ላይ ከትምህርት ቤት ማህበረሰቦች ጋር ጊዜውን-የጠበቀ ግንኙነትን ለማድረግ - ይሰራል (በዚያኑ-ቀን ላይ ማድረግ የተመረጠ-ነው/same day preferred)። የግንኙነቶች-ማድረጊያ ቡድን (Communications Team) የሚከተሉትን፣ ያደርጋል:

  - የቅጥር-ሁኔታው/employment statusን (አስተዳደራዊ-ፈቃድ/administrative leave፣ የለቀቀ/separation፣ ወዘተ... መሆንን) እና ያለውን-የስራ ድርሻ/positionን- ማረጋገጥ፤
  - ለትምህርት ቤቱ ስለሚሰጠው የእርዳታ ደረጃ፣ ከአዕምሮ ጤና (Mental Health) ቡድን ጋር ለማረጋገጥ እና ለማጋራት - ማግኘት፣ ይህ ሁኔታ ካለ (if applicable)፤
  - ክስተቱ የተመራ-መሆኑን በግንኙነት-ከመግለጽ የሚከለክለው ሌላ ምንም አስጊ-ነገሮች አለመኖራቸውን ለማረጋገጥ፣ ከ'MPD' ጋር ወይም ሌላ ተገቢ-ከሆነ የህግ-አስከባሪ ኤጀንሲ ጋር መማከር፤ እና
  - ከ'MPD' ጋር ወይም ከሌላ ተገቢ-ከሆነ የሕግ-አስከባሪ ኤጀንሲ ጋር - መያዝና-እስራትም(arrest) የተደረገ-መሆኑንና አለመሆኑን ማረጋገጥ፤ የሚመለከተው-ከሆነ/if applicable።

የግንኙነት-ማድረጊያ ቡድኑ (The Communications Team) በተጨማሪም፤ እንደየ-አስፈላጊነቱ - በ'Blackboard Connect' ኢሜል አማካኝነት፣ ለትምህርት ቤቱ ማህበረሰብ - የመልዕክት ማሰራጫት ድጋፍን ይሰጣል፤ እና ርዕሰ-መምህራኖችም በሚነገት-ቦርሳ/backpack ውስጥ ወደ መኖሪያ-ቤት በሚላክ ደብዳቤ (በታሸገ ፖስታ/sealed envelope) አማካኝነት - ለቤተሰቦች ሊያስተላልፉም ይችሉ ይሆናል። **ርዕሰ-መምህራኖች፤ ከትምህርት-አሰጣጥ ዋና-ተቆጣጣሪያቸው (Instructional Superintendent) ከሚሰጣቸው-ድጋፍ ጋር፣ የማህበረሰቡን ስጋቶች እና ጥያቄዎች ያስተላልፋሉ።**